Ethiopian People´s Revolutionary Party (EPRP)

*የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ)*

ነሐሴ 10 ቀን 2002 ዓ.ም.

## *በአውሮፓ የኢሕአፓ አህጉራዊ ፓርቲ ኮሚቴ*
## *አመታዊ መደበኛ የአባላት ጠቅላላ ጉባኤውን አካሄደ!!*

በተለያዩ የአውሮፓ ሀገራት የሚገኙ የኢሕአፓ ፓርቲ ኮሚቴ አባላት መደበኛ አመታዊ ጠቅላላ ጉባኤያቸውን ከነሐሴ 7 እስከ 9 ቀን 2010 ዓ.ም. ብዙሃኑ አባላት በተገኙበት የአህጉራዊ ፓርቲ ኮሚቴውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ እድገትና ድክመት በስፋት ከዳሰሰ በኋላ የመፍትሄ ውሳኔዎችንና አዲስ የሥራ አስኪያጅ አባላትን በመምረጥ በተሳካ ሁኔታ ተጠናቋል።

እነዚህ ከጀርመን፣ ከኖርዌይ፣ ከእንግሊዝ፣ ከፈረንሳይ፣ ከስዊዝ፣ ከስዊድን፣ ከዴንማርክና ከሆላንድ የተሰባሰቡ በርካታ አባላቱ ላለፉት 38 አመታት የተሰዉትንና በሞት የተለዩትን ውድ ጓዶቹን በሕሊና ፀሎት በማድረግ ያስታወሰው ይህ ጉባኤ ያለፈውን የሁለቱን አመት የሥራ ሃላፊነት ከተረከበው ዞናል ኮሚቴ የቀረበላቸውን ዘገባ ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ሀገራዊ ፓርቲ ኮሚቴም ለጉባኤው ያቀረቡትን ሪፖርቶች በስፋት የመረመሩበትና ያጤኑበት ከመሆኑ ሌላ በርካታ ግንዛቤውችንም የጨበጡበት ጉባኤ ነበር። ጉባኤው በአውሮፓ የድርጅቱ መዋቅር ድክመትንና እድገትንም በጥሞና የመረመረበት ሲሆን ተጠናክሮ በሚገኝበት በይበልጥ እንዲጠናከር፣ በደከመበት አካባቢ ደግሞ የድክመቱን ሁናቴ በጥሞና መርምሮ የመፍትሄ እርምጃዎችን ጠቁሞ ተግባራዊ በማድረግ በመሆን የትግሉ ደጀንነታቸውን በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀጥሉ መመሪያና ማሳሰቢያ ያስተላለፈበትም ነበር።

ይህ በአውሮፓ አህጉራዊ የኢሕአፓ ፓርቲ ኮሚቴ አባላት ጠቅላላ ጉባኤ የተካሄደው በቅርቡ በተጠናቀቀው የምርጫ ቧልትና የመለስ አገዛዝ በ99.6 በመቶ በማሸነፍ ለሚቀጥለው አምስት አመት መንግሥት ለመመስረት የሚያስችለኝ የሕዝብ ይሁንታ አግኝቻለሁ እያለ መጠነ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ እየነዛ በሚገኝበት በመሆኑ ጉባኤው የኢትዮጵያን የፖለቲካ፣ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታና እንዲሁም ወቅታዊ ድርጅታዊ፣ አለም አቀፋዊና የጎረቤትና የአካባቢያዊ ዜናዎችንም በስፋት ለመዳሰስ የቻለበትም ጭምር ነበር። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በተለይ በእርሻ መሬት፣ የአባይ ወንዝን ተንተርሰው ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በተለያዩ ደረጃዎች በሀገራችን የሚንቀሳቀሱ የባዕዳን ኃይሎች ከመለስ አገዛዝ ጋር ስላላቸው የጠበቀ ግንኙነት በኢትዮጵያ ህዝብ ትግል ላይ ያላቸውን ወደፊትም ሊኖራቸው ስለሚችለው አሉታዊና አዎንታዊ ሁኔታ በጥልቀት ያየበትም ጭምር ነበር። በጎረቤት ሶማሊያና ደቡብ ሱዳንም ያለው የፖለቲካ ውጥረትንም በጥሞና ተመልክቷል።

EPRP
P.O.Box 73337
Washington DC, 20056
USA
Tel. 202-291-4217 Fax 202-291-7645

E-mail : ESPIC@aol.com
Website: www.EPRP.com

EPRP
BP 22
Bois colombes 92270
France

ተጨባጩ ሁኔታ የመለስ አገዛዝ እንደሚያወራው ሳይሆን የበርካታው ሕዝባችን የፖለቲካ፡ ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ ነፃነቱ በመለስ አገዛዝ እየተረገጠበት፡ መሰረታዊ የሆኑ አገልግሎቶች የማያገኝበት በርካታው ሕዝባችንም አሁንም የባዕዳንም ምፅዋት ጠባቂ ለመሆን የተገደደበት፡ በከተማም ሆነ በገጠር መሬቶቹ የሚነጠቅበት፡ በሙስና መስፋፋትም በአስከፊ የድህነት አረንቋ ተቀፍድዶ፡ የእለት ተለት ኑሮውን ለማሸነፍ በማይችልበት አሳዛኝና አስቃቂ ሁኔታ ላይ የመገኘቱ ጉዳይ ከምንጊዜውም በላይ በጣም እያሳሰበው ያለ በመሆኑ ይህንን የጭንቀትና የበደል ኑሮ ለመግታትና ተገቢውንም መፍትሄ ለመስጠት መደራጀት እየተደራጁም ተጠናክሮ መታገል ወሳኝ እንደሆነ ከፍተኛ አፅንዖት የሰጠበት ነበር። በመሆኑም ኢሕአፓ በሀገር ቤት እያደረጋቸው ያሉትን የተለያዩ እንቅስቃሴዎች ለማጠናከር በሚደረገው ርብርቦሽ የበኩሉን አስተዋጽዖ ለማሳደግ ቃል ኪዳኑን ያደሰበትና የትግሉ ነው ሕይወቴ የሚለው መፈክሩን በከፍተኛ ወኔ ያስተጋባበትም ነበር።

ጉባኤው ድርጅታዊ ነክ የሆነትን የወጣቱን፡ የሴቶችን፡ መንግሥታዊ ያልሆኑ የሲቪል ድርጅቶችን፡ የሰብአዊ መብቶች እንዲከበሩ ስለሚደረጉት እንቅስቃሰዎችና ሌሎችም በርካታ ሁኔታዎችንም ሰፊ ጊዜያት ሰጥቶ በጥልቀት መርምሯል። ውሳኔዎች ወስዷል። መመሪያዎችንም አስተላልፏል።

ሀ. የኢሕአፓ የወጣት ክንፍ ወክንድ ለመመስረቱ ከፍተኛ አድናቆቱን የገለፀው ይህ ጉባዔ በተለይም ወክንድ በቅርቡ ያከናወናቸው እንቅስቃሴዎች አበረታታች መሆናቸውን በመገንዘብ በይበልጥ እንዲጠናከር የበኩሉን ድጋፍና ትብብር ለማጎልበት መመሪያዎችን የወሰነበት፡ ለኢትዮጵያዊያን ወጣቶችና ለድርጅቱ ደጋፊዎች ከኢሕአፓ ወጣት ክንፍ ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ግንኙነቶችን በመፍጠር የነፃነት ትግሉን እንዲጎለብትና እንዲዳብር የተቻላቸውን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ ወገናዊ ጥሪ ያስተላለፈበትም ነበር።

ለ. ያለ ሴቶች ቀጥተኛና ሙሉ ተሳትፎ ለነጻነት፡ ለዴሞክራሲና ለመብት መከበር የሚደረገው ትግል ግቡን የማያሳካ መሆኑን ያጠናከረው ይህ ጉባኤ በዚህ በኩል አለም አቀፍ የኢትዮጵያ ሴቶች ድርጅት ይህንን ክፍተት ለመሙላት ድርጅታዊ ነፃነቱን በመጠበቅ እያደረጋቸው ስላላቸው እንቅስቃሴዎች ያለውን አድናቆቱን ገልጿል። የሴቶች ሚና በሁሉም መልክ እንዲጎለብት ያገራችን የፖለቲካ ድርጅቶች የሴቶችን ተሳትፎ ማሳደግ አለባቸው የሚል ፅኑ እምነቱን የገለፀው ይህ ጉባኤ የኢሕአፓ ሴቶች አባላትም በተለያዩ በተለይም በአለም አቀፍ የኢትዮጵያዊ ሴቶች ድርጅት ውስጥ አባል በመሆን ሊኖራቸው የሚችለውን ቅርበት፡ ድጋፍና ትብብር ይበልጥ እንዲያጠናክሩ አሳስቧል።

ሐ. ከተቋቋመ 15ኛ አመቱን የያዘው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ (ኢፖእአኮ) በኢትዮጵያ በመለስ አገዛዝ እየተደረጉ ያሉ የሰብአዊ መብት መጓደልንና የፖለቲካ እስረኞች ሁኔታ፡ የዜጎች ደብዛ መጥፋትና የደረሱበት አለመታወቅ ሁኔታዎችን በማጋለጥና በመታገል አኩሪ ውጤትን እያስመዘገበ ያለ መሆኑን በማጤን በተለይም የጉድለቶቹና የጥሰቶቹ አይነትና ብዛት እየጨመረ፡ የፍትህ ጉድለትና የመልካም አስተዳደር እጦትም እያስከተሉት ያሉት ችግሮች ተደምረውበት ብዙሃኑ ዜጎቻችን ይህ ነው የማይባል ስቃይና በደል እንዲሸከሙ ከማድረጉም በላይ ከቁያቸው ተፈናቅለው ለስደት የተዳረጉት ቁጥራቸው ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ መሆኑን ከሚወጡት ይፋዊ መግለጫዎች ተገንዝቧል። ይህ በዜጎች ሕይወት የመቀለድ አባዜ ሀገርን ለአደጋ፡ ሕልውናዋንም ለከፍተኛ ጉዳት የሚዳርግ መሆኑን የተገነዘበው ጉባኤ በሰብአዊ መብት መከበር እየተንቀሳቀሱ ያሉ ሀገር በቀል ድርጅቶች በተለይም የፖለቲካ

ወገንተኛነትን ሳያንፀባርቅ ለሚንቀሳቀሰው ለኢፖእአኮ ያለውን አክብሮትና አድናቆት በመግለጽ ለዚህ ድርጅት የሚደረገው ትብብርና እርዳታ በከፍተና ደረጃ እንዲቀጥል ጥሪውን አስተላልፏል።

መ. የኢትዮጵያ ሕዝብ ዋናው ግቡ መሰረታዊ የሆኑት የዜግነት እኩልነቱን በማረጋገጥ ላይ በተመሰረተ የሀገሩን ሕልውና ከአደጋ በማዳን ነፃነቱንና መብቱን ማስከበር ሲሆን ለዚህ አላማ ስኬታማነት የሚታገሉ ድርጅታዊ ሕልውናና በሀገር ቤት ለሚንቀሳቀሱ ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ኢ.ሕአፓ በቅርቡ ያቀረበው የውይይት ጥሪ መግለጫ የወቅቱን ተጨባጭ ሁናቴና ወደፊትም መደረግ ያለበትን እንቅስቃሴ የሚጠቁም መሆኑን ዳግም ያጤነው ይህ ጉባኤ ለዚህ ቅንና ወሳኝነት ላለው አላማ የኢ.ሕአፓ አባላት በሀገርና በውጭ ሕዝብን ለማደራጀት የሚያደርጉት እንቅስቃሴ አኩሪነቱን በመገንዘብ በበለጠ ለማጠናከርና ለማስፋት ሁሉም ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆኑ ክፍሎች ጥሪውን በጥሞና ተቀብለው ይህንን ታሪካዊ ኃላፊነት ለመሸከምና ከግብ ለማድረስ ኢ.ሕአፓን በዚህ በኩል እንዲተባበሩት የአደራ ጥሪውን አስተላልፏል።

ሰ. በቅርቡ በኢ.ሕአፓ ላይ እየተደረገ ያለውን የጥላቻ ዘመቻና የጀግንነት ታሪኩን ጥላሸት ለመቀባትና ብሎም ከሕዝብ ለመነጠል የሚደረገውን ዘመቻ በስፋትና በአንክሮ ከዳሰሰ በኋላ የድርጅቱን እውነተኛ ታሪክ እየጠበቁና እየተንከባከቡ ለአዲሱ ወጣት ትውልድ ለማስረዳትና ግልጽ ለማድረግ በከፍተኛ ደረጃ መሰማራት ሁኔታው የሚጠይቅ መሆኑን አጽንዖት ተሰጥቶበት ተግባራዊ እንዲሆን መመሪያዎችንና ውሳኔዎችንም አስተላልፏል። በጽሁፍም ቀርበው በድርጅቱ ሰነድነትና ለታሪክ መዛግብትነት መጠቀሚያ እንዲሆኑ ከፍተኛ ርብርቦሽም እንዲደረግ ወስኗል።

ይህ ቀደም ብለው ከተደረጉት ጉባኤዎች ለየት ባለ መልክ ሰፋ ያለ ጊዜ ወስዶ ሌሎችም በርካታ የተለያዩ ፖለቲካዊና ድርጅታዊ ነክ ውሳኔዎችን በማሳለፍ ለሚቀጥለው የሁለት አመት የሥራ ዘመንም የድርጅቱን እንቅስቃሴ በኃላፊነት የሚመሩ የዞናል ኮሚቴውን አባላት መርጦ በመጨረሻም የማሳረጊያና የማጠቃለያ የቀረበለትን ንግግር አዳምጦና መልካም የሥራ ዘመን ለሁሉም አባላቱ በመመኘት በተሳካ ሁናቴ የተጠናቀቀው (ይህ ጉባኤ) የአባላቱን የትግል ወኔና መንፈስን በአዲስ መልክ ተሃድሶ የሰጠና ያጠናከረ መሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም።

ለመብት መከበርና ለነጻነት የሚደረገው ትግል በፅናት በቆራጥነት ይቀጥላል!!

ኢ.ሕአፓ ያቸንፋል!!